# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 318 ሰኔ 6 2006 ገጽ 1


ግንቦት 7 የፍትህና የዴሞክራሲ ንቅናቄ አገራችን ይህን ሁሉ ግፍና መከራ ማስተናገድ እንዲበቃት ልጆቿ ተባብረን እንድንነሳ ደጋግሞ ጥሪውን ያቀርባል።

ለወያኔ የተመቸነው በየተራ ለመጠቃት አንዱን ብሄረሰብ በሌላው በማስፈራራትና ጥርጣሬ በመንዛት ለመግዛት የቀየሰው ዘዴ ሰለባ መሆናችን ነው።

ግንቦት 7 ንቅናቄ፤ የወያኔ የግፍ ቀንበር እንዲሰበር ሰፊ ህብረት ፈጥረን ከመታገል ውጪ አማራጪ የለንም ይላል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በሐረር ከተማ የተገኘው የጅምላ መቃብር ግጭት ማስነሳቱ ተገለፀ

በሐረር በጅምላ የተቀበሩ ሰዎች መቃብር መገኘቱን ተከትሎ ህዝቡ ከነፍሰ በላው የወያኔ አገዛዝ ጋር ግጭት ውስጥ በመግባቱ በአካባቢው ከፍተኛ ውጥረት መንገሱን ምንጮቻችን ከላኩልን መረጃ ለማወቅ ተችሏል።

በሐረር ከተማ አቅራቢያ በሚገኘው ሐማሬሳ ቀበሌ ውስጥ ሰሞኑን በቁፋሮ ላይ የነበረ አንድ የግሪደር ሹፌር የተከማቹ አስከሬኖችን ማግኘቱ ታውቋል። ከተገኙት አስክሬኖች መካከል አብዛኞቹ ምንም አይነት የመበስበስ ምልክት ያልታየባቸው ሲሆን ግለሰቦቹ በፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ ዘመን የተገደሉ መሆናቸውን ያሳያልም ተብሎአል። አንደኛው ሟች እጆቹን ወደ ሁዋላ ለፊጥኝ ታስሮ የተገኘ ሲሆን ሌላው ደግሞ አይኖቹ በጨርቅ መሸፈናቸውን የአይን እማኞችን ዋቢ በማድረግ ዘጋቢያችን ከቦታው የላከልን መረጃ ያመለክታል።

ህዝቡ አስከሬኖቹ እንዳይነሱ እና ምርመራ እንዲካሄድባቸው ጥያቄ ቢያቀርብም፣ የአካባቢው የነፍሰ በላው ህወሓት ቅጥረኞች ፈቃደኛ ባለመሆናቸው አስከሬኖቹ ሳይመረመሩ ከቦታው እንዲነሱ መደረጉም ታውቋል። በተለይ በቅርቡ የተገደሉ ናቸው የተባሉ የሁለት ግለሰቦችን አስከሬን ማንነት ለማወቅ በተደረገ ጥረት ህዝቡ ከቅጥረኛ የወያኔ ፖሊሶችና የአካባቢው ሹማምንት ጋር ግጭት ውስጥ መግባቱን ያደረሰን ዘጋቢያችን ምናልባትም ግጭቱ ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ወያኔ አሁንም አማርኛ ተናጋሪዎችን ማፈናቀሉን አላቆመም

የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ በጋምቤላ ክልል ከቴፒ ከተማ ወጣ ብሎ በሚገኘው ጎደሬ ልዩ ስሙ ዳንቻ ተብሎ በሚጠራው አከባቢ ለበርካታ ዘመናት ይኖሩ የነበሩና በተለያየ ስራ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ አማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ኢትዮጵያውያንን ማፈናቀል መጀመሩን ከአከባቢው የደረሱን መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ካለፈው ሳምንት የጀመረው የማፈናቀል ድርጊት በአሁኑ ወቅት ወደ ግጭት ተለውጦ የጉጅሌው ወያኔ ቅጥረኞች ሃይልን በመጠቀም ላይ መሆናቸው የታወቀ ሲሆን በአከባቢው የሚኖሩ አባወራዎች ንብረቶቻቸውን በመተው ሽሽት ላይ መሆናቸው ታውቋል። ድርጊቱን ተከትሎ በአካባቢው ትምህርት ቤቶች እና የመንግስት መስሪያ ቤቶች የተዘጉ ሲሆን በአከባቢዎቹ የፈሰሰው የወያኔ አጋዚ ጦር ግጭቱን በማባበስ ዜጎችን በማስጨነቅ ላይ መሆናቸው ታውቋል።

በሌላ ዜና ትላንት ሰኔ 4 ቀን በባህር ዳር ከተማ ከመልካም አስተዳደር ችግሮች ጋር በተያያዘ የባጃጅና ታክሲ አሽከርካሪዎች ከጧቱ 1:00 ጀምሮ የስራ ማቆም አድማ መምታታቸው የታወቀ ሲሆን አድማውን ተከትሎ የጉጅሌው ወያኔ ቅጥረኛ የፌደራል ፖሊሶች አድመኞችን ለማሰር ሲቅበዘበዙ መዋላቸውና በርካታ ወጣቶችም ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ወያኔ ምርጫውን አስታኮ ቤቶችን ለያከፋፍል ነው

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ በሚቀጥለዉ አመት ይጠናቀቃል ብሎ ለህዝብ ቃል የገባዉ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ በአብዛኛው ዘርፎች እንዳልሳካለት በግልጽ የሚታወቅ ሆኖ ሳለ ይህ ዘረኛ አገዛዝ የመጪውን ዓመት ምርጫ ተከትሎ የኢትዮጵያን ህዝብ ለማታለል የተለመደ የቅጥፈት ስራዉን እየሰራ መሆኑ በመነገር ላይ ነዉ። በዚህም መሰረት የሕዝብ ድጋፍ ያስገኙልኛል ብሎ ያሰባቸዉን ስራዎች እስከ ምርጫዉ ግዜ ድረስ ለማከናውን በአቅዶ በመንቀሳቀስ ላይ መሆኑን ውስጥ ምንጮች ገለጹ:፡ በዚሁ ዕቅድ መሠረት የመኖሪያ ቤት ለማግኘት ወደ 800ሺ ሕዝብ የተመዘገበበት በአዲስ አበባ ከተማ በያዝነው ወር እና በነሐሴ ወር 40 ሺኮንዶምኒየም ቤቶችን እጣ ለማውጣትና በዚህም ድጋፍ ለማግኘት ታቅዶአል።

በተመሳሳይ ሁኔታ እስከ ታህሳስወር 2007 ባሉት ጊዜያት እንዲሁወደ 40 ሺ የሚሆኑ ተጨማሪ ቤቶችን ለተጠቃሚዎች ለማስተላለፍ ታቅዶ እየተሰራ መሆኑንምንጮቻችን ጠቁመዋል። ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## በአጋዚ ጦር በግፍ የወደቁት ወገኖቻችን ቀን በመላዉ ኢትዮጵያ ታስቦ ዋለ

የሕዝብ ድምጽ ይከበር በማለት የ1997ቱን ምርጫ ተከትሎ በመጣው ሰላማዊ የሕዝብ ጥያቄ እና ጥያቄውን አልሰማም ብሎ ከዳር ቆሞ በነበረው ሕወሃት መራሹ ወያኔ መካከል የተፈጠረውን አለመግባባት ቅልቡ ጦር አግአዚ ሕዝብን በጥይት በመጨፍጨፍ ምላሽ የሰጠበትና በመቶዎች ገድሎ ሽዎችን ያቆሰለበት እንዲሁም ብዙዎችን ወደማጎሪያ ጣቢያ ያስገባበት 9ነኛ ዓመት ሰኔ 1 በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ በሚገኙ ኢትዮጵያዉያን ታስቦ መዋሉ ተሰማ። እድሜን ጾታንና የአካል ጉዳተኞችን ሳይቀር የጥቃቱ ሰለባ ያደረገው ይህ በጠራራ ፀሐይ የተፈጸመው ጭፍጨፋ፤ የምርጫ ድምጻችን ይከበር በማለት በሰላማዊ መንገድ የወጡ ሰላማዊ ሰዎች ላይ መፈጸሙ ሳያንሰው፤ ሟቾቹ ባንክ ሊዘርፉ የሞከሩና ከወታደሮች ላይ መሳሪያ ሊነጥቁ የሞከሩ ወሮ በሎች ናቸው በማለት በወያኔ ሚዲያ መሰራጨቱ ብዙዎችን እንዳበሳጨና እስካሁንም ድረስ የውስጥ ጸጸት ሆኖ እንዳለ ብዙዎች ይስማማሉ።

ወያኔ በምርጫ ከተሸነፈበት ግንቦት 7 97 ዓ/ም ጀምሮ ባለራእይ በሚሉት ፈሽስት መለስ ዜናዊ ትእዛዝ ሙሉ በሙሉ በወታደራዊ እዝ ስር ትገኝ የነበረችው ሀገራችን በተለይ ከሰኔ 1 ጀምሮ በነበሩት ጥቂት ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## በአዲስ አበባ የህዝብ መፈናቀል እንደሚቀጥል መረጃዎች አመለከቱ

ለዜጎች ምንም ደንታ የሌለዉ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ በአንድ በኩል አዲስ አበባን ለማሳደግ በሚል ገበሬዎችን እያፈናቀለ በሌላ በኩል ደግሞ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ማደስና ፕላን ዝግጅት በሚባለው ፕሮግራሙ በመሃል አዲስ አበባ የሚኖሩ ነዋሪዎችን በስፋት በማፈናቀል ላይ እንደሚገኝ አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢዎች በላኩልን ዜና ገለጹ። ወያኔ ለተፈናቃይ ገበሬዎችም ሆነ ቤታቸዉ ለሚፈርስባቸዉ ዜጎች ምንም ያክል ካሳ የማይከፍል በመሆኑ የተፈናቃዮች ዕጣ ፈለግ ልመና መሆኑን ብዙዎች በመናገር ላይ ናቸዉ። በተለይ አዲስ አበባን ለማሳደግ በሚል ሰበብ የሚገናቀሉት ገበሬዎች በከፍተኛ ስቃይ ላይ መሆናቸዉን ለማወቅ ተችሏል።

አካባቢን መልሶ የማልማት ገጽታ አለው በሚባለው ሥራ ውስጥ ዘንድሮ ከተካተቱ አካባቢዎች መካከል በካዛንቺስ 26 ሄክታር፣ በደጃች ውቤ 11.6 ሄክታር፤ በሸበሌ ሆቴል ዙሪያ 10.4 ሄክታር፣ አሜሪካንግቢ 16 ሄክታር፣ በአፍሪካ ህብረት ቁጥር 2 ወደ 15 ሄክታር፣ ተክለሃይማኖት 33 ሄክታር፣ አሮጌው ቄራ ቁጥር 1 እና 2 እንደቅደም ተከተሉ 14 ሄክታርእና 54 ሄክታር፣ ባሻወል ዴቄጥር የፓርላማ ማስፋፊያ 4 ሄክታር ቤት የማፍረስ እቅድ መኖሩን ተከትሎ በአንዳንድ አካባቢዎች ለነዋሪዎች ካሳ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ተሸለመ

እሱ እራሱ የለየለት ጅምላ ገዳይ ሽብርተኛ ሆኖ ሰለማዊ ዜጎችን እሰበሰበ ሽብርተኛ ናችሁ እያለ የሚያስረዉ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ በአለም አቀፍ መድረኮች ላይ እየተዋረደ መሆኑን የሚያሳዩ ብዙ ሁኔታዎች በመታየት ላይ ናቸዉ። ለምሳሌ ወያኔ ሽብርተኛ ነህ ብሎ 18 አመት የፈረደበት እዉቁ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ የ2014 "የጎልደን ፔን ኦፍ ፍሪደም" ሽልማት አሸናፊ ሆኖ ተሸልሟል። እስክንድር ነጋ ሽብርተኛ ከተባለ በኋላ አለም አቀፍ ድርጅቶች ጀግና ብለዉ ሲሸልሙት ይህ ሁለተኛ ግዜዉ ነዉ። ወያኔ ሽብርተኛ ብሎ ካሰራቸዉ የህዝብ ልጆች ዉስጥ ርዕዮት አለሙና ዉብሸት ታየም እንደ እስክንድር ነጋ አለም አቀፉ ህብረተሰብ ጀግና ብሎ ሸልሚቸዋል። በጣሊያን ቶሪኖ በተካሄደው የሽልማት ስነ-ስር ዓት ላይ እስክንድርን ወክሎ ሽልማቱን የተቀበለው በቃሊቲ እስር ላይ የነበረው ስዊድናዊ ጋዜጠኛ ማርቲን ሽብዬ ነው። ነነ"ምኞቴ ይህን ሽልማት እኔ እንድቀበለው አልነበረም" በማለት ንግግሩን የጀመረው ማርቲን፣ "ዛሬ ጠዋት ስነሳ ምናለ:-" ተፈታሁኮ፤ ሽልማቱን እኔ ራሴ ልቀበል እመጣለሁ" የሚል ስልክ ከአዲስ አበባ በስልክ ብሰማ ብዬ ተመኝሁ" ብሎአል።

"ይህ ግን አልሆነም፤ ከሰ ዓታት በፊት እስክንድር ነጋ በዱላቸው የታሰሩባትን ክፍል ግድግዳ እየመቱ በማይክራፎን "ቆጠራ!ቆጠራ!" እያሉ በሚጮኹ የወህኒ ጠባቂዎች ድምጽ ነው ከመኝታው የተነሳው" ያለው ማርቲን፣ የሙያ ባልደረባውን ወክሎ ሽልማቱን ሊቀበል በስፍራው መገኘቱን ግልጾአል። "ምንም እንኳዋን ከሲያ እስር ቤት ነጻ እንደሆንኩ ባስብም፤ ከትስታዎቹና ከእስር ቤቱ ድምጾች ፈጽሞ ነጻ ልሆን አልችልም"ሲልም ማርቲን ተናግሮአል።

( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## የወያኔ ግፍ ለከቱን አልፏል!

የወያኔ ጉጅሌ ራሱ ከሳሽ፣ ፖሊስና ዳኛ ሆኖ በሚገዛት ሀገራችን ውስጥ የሚያካሂደው ግፍ አንድ ህዝብ ሊሸከመው ለሚችለው በላይ ሆኗል።

የወያኔ ሹማምንትና በዘር ለዝርፊያ የተሰማራው ድርጅታቸው በቅርቡ ደግሞ ስዘርፍ አያችሁኝ በሚል ቁጣ ከአንደበታቸው በላይ ምንም ባልታጠቁ የኦሮሞ ተማሪዎች ላይ ከአካሄደው ጅምላ ጭፍጨፋ አልፎ ግለሰብ ተማሪዎችን በማሳደድ ሰቆቃ መፈጸሙን ቀጥሎበታል። በዚህ ሰአት በርካታ ተማሪዎች በታወቁና ባልታወቁ እስር ቤቶች ታጉረዋል። ብዙዎቹ ከትምህርት ገበታ ካላንዳች ጥያቄ ተባረዋል እየተባረሩም ይገኛሉ።

ከወያኔ ግፎች ሁሉ በእጅጉ የሚዘገንነው ሌሎችን በመወንጀል ማሰቃየትና መግደል በፈለገ ቁጥር ራሱ ወንጀል ከፈጸመ በኋላ ወንጀሉን በሌሎች ላይ ለማመኻኘትና ለመቅጣት የሚጠቀሙበት የሃሳብ ዘዴ ነው።

በአለምያ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በተሰበሰቡበት አዳራሽ ውስጥ የደህንነት አባሎች ቦንብ አፈንድተው ጉዳት ካደረሱ በኋላ የሚፈልጓቸውን ወጣቶች ቦንብ ሲያፈነዱና ሲጠምዱ ያዝናቸው በማለት ከዚህ በፊት በዊክሊክ መረጃ እንደተለቀቀው የተለመደ በሰው ልጆች ላይ ሰቆቃ ይፈጽማሉ። ሌላው ቀርቶ ቦምብ አፈነዱ ተብለው የተከሰሱት ተማሪዎች በገዛ ጓደኞቻቸው ላይ ቦምብን የሚወረውሩበት ምክንያት የላቸውም።

ወያኔ ተማሪዎቹን አረመኔና እብድ ለማስመሰል የሰራው የራሱ ትንሽዬ ድራማ ወይም ሌላኛው አኬልዳማ መሆኑ ግልጽ ነው።

ወያኔ ደግሞ እንዲህ አይነት የወሮበላ ስራ እንደሚሰራ እንዳላዩ የሚያዩት ለጋሽ ሀገሮች ሁሉ ያጋለጡት፣ የሚያውቁት የአደባባይ ሚስጥር ከሆነ ሰንበቷል።

በዚህ መሰሪ ወንጀል ያዝናቸው ብለው ከአሰሯቸው ተማሪዎች ውስጥ የቦኮ ትቤ ተወላጅ የሆነ ኑረዲን ሃሰን የተባለ የአለመያ ዩኒቨርስቲ ተማሪ በድብደባ አሰቃይተው ከገደሉት በኋላ ራሱን ገደለ ብለው አስክሬኑን ለቤተሰቦቹ ሸጠውታል:: በአሁኑ ወቅት ብዙ ተማሪዎች የደረሱበት እና የገቡበት ተፍጧል።

ይህ ሰቆቃ መጠኑን አልፏል! ግፍ በዚሁ እንዲቀጥል ከሆነ ደግሞ መቆም የሚችልበት ተግባር ባለመፈጸማችን ሁላችንም የዚያች ሀገር ልጆች ከታሪክ ወቀሳ እና ከህሊና ጸጸት አናመልጥም። ወያኔዎች በዘር ከፋፍለው በየተራ ስለሚያጠቁን ነው ይህ የሽብር አገዛዛቸው እድሜ ያገኘው። ይህን አደገኛ ክፍተት ካልዘጋነው መከራው ቀጥሎ ያሰቃየናል።

ግንቦት 7 የፍትህና የዴሞክራሲ ንቅናቄ አገራችን ይህን ሁሉ ግፍና መከራ ማስተናገድ እንዲበቃት ልጆቿ ተባብረን እንድንነሳ ደጋግሞ ጥሪውን ያቀርባል።

ለወያኔ የተመቸነው በየተራ ለመጠቃት አንዱን ብሄረሰብ በሌላው በማስፈራራትና ጥርጣሬ በመንዛት ለመግዛት የቀየሰው ዘዴ ሰለባ መሆናችን ነው።

ግንቦት 7 ንቅናቄ፤ የወያኔ የግፍ ቀንበር እንዲሰበር ሰፊ ህብረት ፈጥረን ከመታገል ውጪ አማራጪ የለንም ይላል።

የወያኔ ግፍ ይብቃ!

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## በሐረር ከተማ የተገኘው የጅምላ መቃብር

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

እየከረረ ወደ አጎራባች አካባቢዎችም ሊዛመት እንደሚችል ተጠቁሟል። በቅርብ እንደተገደሉ የተነገረላቸው ሁለቱ ትኩስ አስክሬኖች በቅርቡ በሃረር ፖሊስ ጣቢያ ታስረው አድራሻቸው መጥፋቱ የተነገረው ሁለት ወጣቶች ሊሆን እንደሚችልም በስፋት እየተነገረም እንደሚገኝም ለማወቅ ተችሏል።

ነፍሰ በላው ህወሓት በሐረር ከተማ በሰዎች ላይ ግድያ በጅምላና በተናጠል በተደጋጋሚ መፈፀሙ የሚታወቅ ሲሆን በአገዛዙ ትዕዛዝ በስውር እየገደሉ ድብዛቸው የሚጠፋ ሰዎች በመበራከቱ ህዝቡ በጋራ የመኖር ዋስትናችን አደጋ ላይ ወድቋል በማለት ከአገዛዙ ጋር ግጭት ውስጥ መግባቱ ታውቋል። ግጭቱን ተከትሎ የአካባቢው የፋሽስቱ ወያኔ ቅጥረኛ ካድሬዎች የህዝቡን ተቃውሞ ለማፈን እየተቅበዘበዙ ሲሆን ከፍተኛ ቁጥር ያለው ጦር ወደ አካባቢው እንዲንቀሳቀስ ከበላይ የህወሓት ሹማምንት ትዕዛዝ መተላለፉንም የውስጥ ምንጮቻችን ካደረሱን መረጃ ለማወቅ ተችሏል።

## ወያኔ አሁንም አማርኛ ተናጋሪዎችን ማፈናቀሉን

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ታፍሰው መታሰራቸው ታውቋል። የአካባቢው ዘጋቢያች ያደረሰን መረጃ እንደሚያመለክተው የአሽከርካሪዎቹ አድማ መንስኤ ፋሽስቱ ወያኔ በከተማዋ ያንሰራፋው ስርአት አልበኝነት የወለደው የመልካም አስተዳደር ችግር መሆኑ የታወቀ ሲሆን አሽከርካሪዎቹ በተለይም ከትራፊክ ፖሊስ፡ ከመንገድ ትራንስፖርት እና ከባጃጅ ማህበራት እየደረሰባቸው የሚገኘው በደል ለአድማው እንዳነሳሳቸው ለማወቅ ተችሏል። የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ለጥያቂያችን ምላሽ እስካልሰጠ ድረስ የስራ ማቆም አድማው ይቀጥላል ያሉት ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው አንዳንድ አሽከርካሪዎች በተለይም የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ ያስከተለውን ስርአት አልበኝነት በጋራ ልንዋጋ ይገባል በማለት በክልሉ የሚገኙ አሽከርካሪዎች ድጋፋቸውን ይሰጧቸው ዘንድ ጥሪ ማስተላለፋቸው ታውቋል።

## ወያኔ ምርጫውን አስታኮ ቤቶችን

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ከዚህ ቀደም የቤቶቹ ግንባታ 50 በመቶ እንኳዋን ሳይጠናቀቅ በአየር ላይ ዕጣ እንዲወጣ በማድረግ ዕድለኞች ቤታቸውን እስኪረከቡ እስከ ሁለት ዓመታት ጊዜ ይፈጅ የነበረው ጊዜ አሁን ከምርጫው ጋር በተገናኘ ዕጣው በወጣ ሰሞን ዕድለኞች ቤቱን እንዲረከቡ በከተማዋ አስተዳደር በኩል ጥንቃቄ እንዲደረግ በተሰጠው ማሳሰቢያ መሰረት ለመጀመሪያ ጊዜ እድለኞች እጣው በወጣበት ሰሞን ቤታቸውን ይረከባሉ ተብሎ ይጠበቃል።

በአዲስ አበባ ያለው መኖሪያ ቤት ችግር የኢህአዴግ አባላትም ጭምር በየጊዜው ቅሬታ የሚያቀርቡበትና የሚጋሩት በመሆኑ ገዥው ፓርቲ በጊዜያዊነት በሚወስዳቸው እርምጃዎች ጥገናዊ ለውጥ አገኝበታለሁ ብሎ ማመኑ ተጠቁሞአል። በተለይ በአስተኛና ጥቃቅን የተደራጁ ዜጎች ችግሮቻቸውን ማለትም የብድር፤የመስሪያ ቦታና የመሳሰሉት በአፋጣኝ ተፈትቶላቸው ይህን ኃይል የምርጫ ሠራዊት ለማድረግ መታሰቡም ታውቋል። ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ እጅግ የተለጠጠ የአምስት ዓመት ዕቅዱ በቀጣይ ዓመት መጨረሻ የሚጠናቀቅ ሲሆን በዚህ ዕቅድ መሠረት ይደረስበታል ተብሎ የታሰቡ ስራዎች በአብዛኛው ሳይሳኩ ቀርተዋል። በተለይ ባለፉት ሁለት ዓመታት በቡና ላይ የተመሰረተው ኤክስፖርት መቀዛቀዙ መንግስትን ከፍተኛ ገቢ አሳጥቶታል።

የሰለጠነ የሰው ሃይል እጥረት የፋይናንስ አቅም ውስንነት እንዲሁም ዕቅዱ ሁሉንም ወገን አሳታፊ ባለመሆኑ ምክንያት ከግብርና ወደ ኢንዱስትሪ ይደረጋል የተባለው ሽግግር በአየር ላይ መቅረቱን ምንጮች ይገልጻሉ፡የግል ባለሃብቱን በማሳተፍ ረገድ የታየው ዳተኝነትና በኢኮኖሚ ውስጥ የመንግስትና በገዥው ፓርቲ ስር ያሉ የንግድ ተቋማት ጣልቃ ገብነት መጠናከር ዕቅዱ እንዳይሳካ ትልቅ አስተዋጽኦ ማድረጋቸው ታውቋል። ኢህአዴግ በምርጫ የማሸነፊያ ስትራቴጂው መሰረት ለከተማ ነዋሪዎች መሬት በአነስተኛ ገንዘብ ያከፋፍላል። ለአርሶአደሮች ደግሞ የማዳበሪያ እና የምርጥ ዘር እዳ እፎይታ ይሰጣል።

ኢህአዴግ ይፋዊ ያልሆነ የምርጫ ቅስቀሳውን አጠናክሮ የቀጠለ ሲሆን ፤ በተለያዩ ወረዳዎች በመንቀሳቀስ በአምስት አመቱ ተገኙ ያላቸውን ድሎች በራሱ ካድሬዎች አማካኝነት ህዝቡ እንዲያውቃቸው እየጣረ ነው። በአንዳንድ አካባቢዎች ህዝቡ ኢህአዴግ ካሰበው በተቀራኒ እየተናገረ ሲሆን በቅርቡ በሳምንቱ መግቢያ በደብረብርሃን ከተማ ተካሂዶ በነበረው ውይይት ላይ ህዝቡ በልማቱ ተጠቃሚ አለመሆኑን መናገሩ ታውቋል። በደብረብርሃን የነበረውን ስብሰባ ዜና እና የህዝቡን አስተያየት በነገው ዜና የምናቀርብ መሆኑን ለመግለጽ እንወዳለን።

## የኑረዲን ሃሰን ደም በከንቱ አይቀርም

ጉጅሌዎቹ ኢትዮጵያን መግዛት ከጀመሩ ዘመን ጀምሮ በአገራችን የንፁህ ሰው ደም ሳይፈስ የዋለበት ቀን የለም። ኢትዮጵያችን በየቀኑ የንፁህ ሰው ደም የሚፈስባት አገር ሁናለች። ዜጎችም ይሄን የለመዱት ስለሆነ ሰው ሞተ ሲባል ብዙም አይደነቁም። ጉጅሌዎቹ ደግሞ አንድ ያለፈባት ብሂል አለቻቸው እንዲህ የምትል፤

*ግደሉ ግደሉ ሰው መግደል ይበጃል፤*
*ሰው ያልገደለ ሰው ሲሄድ ያንጎላጃል።*

ይህች የአንድን ማህበረሰብ የስነ ልቦና ቀውስ ደህና አድርጋ የምታሳይ ቅኔ የህወሃቶች ስንቅና ትጥቅ ነች። ይህችን ቅኔ ታጥቀው በየደረሱበት የንፁህ ደም ሲያፈሱ የሂሊና ወቀሳ የለባቸውም። እዚህም ይገድላሉ፤ እዚያም ይገድላሉ። ለህወሃቶች ሰው መግደል ክፉ ነገር አይደለም። ሰው መግደል ለስልጣን የሚያበቃ፤ ስልጣን ላይም እስከ ፍፃሜው የሚያቆይ የጎበዝ ምግባር ነው የሚል የማይናወፅ እምነት አላቸው። ይህን ዕምነታቸውንም የገለጡበትን መንገድ ትንሽ ወደ ኋላ ሂዶ በሃውዜን ህዝብ ላይ ያስፈፀሙትን ጭፍጨፋ ማስታወስ በቂያችን ይሆናል።

ጉጅሌዎቹ ጥልቅ በሆነ የስነ ልቦና ቀውስ ውስጥ ይገኛሉ። ከግል ህይወታቸው ጀምሮ እስከ ጨበጡት የስልጣን እርከን ድረስ ንፅህና የጎደላቸው፤ በንፁሃን ደም እጃቸው የተጨማለቀ ነው።ይህ ነውራቸውም ሁሉንም እንዲፈሩ፤ በሁሉም እንዲደነግጡ አድርጓቸዋል።ከዚህ ፍርሃትና ድንጋጤም ለመላቀቅ የተዘፈቁበት የወንጀል መዓት የሚያስችላቸው አልሆነም። እነርሱም ከጥፋታቸው ተምረው እንደ ሰው ልጅ ለማሰብ ፍላጎቱ የላቸውም። የጉጅሌዎቹ የልብ ድንደና የመፅሃፍ ቅዱሱ የፈርዖንን ልብ ድንደና ይመስላል። የፈርዖንን የመጨረሻ ታሪክ ያየ ግን ልቡን ከማደንደን ይልቅ የህዝቡን ጩኸት መስማትን ይመርጥ ነበር። ይሄም ቢሆን ብልህነትን ይጠይቃል።አገራችን ከተደቀኑባት ብርቱ ተግዳሮቶች መካከል ዋነኛው ጉጅሌዎቹ ብልህነት ያልፈጠረባቸው ሁሉንም በጠብ-መንጂያ እናሸንፈዋለን ብለው ከልባቸው ማመናቸው ነው። ይሄም እምነታቸው ነው በህግ ጥላ ሥር ያሉትን እንኳ ሳይቀር ቀጥቅጠው እንዲገድሉ የሚያደርጋቸው።

በዓለማያ ዩንቨርስቲ ውስጥ ወለጋ ክለብ ተብሎ በሚጠራው አዳራሽ ውስጥ ቦንብ ፈንድቶ ተማሪዎች መጎዳታቸውን የነገረን ህወሃት ነው። ጉጅሌዎቹ እኛ ከመጣን በኋላ ሠላም ሆነ እያሉ በሚያላዝኑበት አገር ውስጥ ይህን መሰሉ እኩይ ተግባር እንደምን ሁኖ ሊፈፀም እንደቻለ በቂ ማብራሪያ የላቸውም። ብዙ ተማሪዎች ከተጎዱ እና ህይወትም ከጠፋ በኋላ ጥፋተኞቹን ያዝኩ ሲልም ያወጀው አሁንም ጉጅሌው ነው። ከተያዙት መካከልም አንዱ ኑረዲን ሃሰን በእስር ቤት እንዳለ ህይወቱን አጠፋ መባሉንም የሰማነው ከጉጅሌዎቹ ነው። በህግ ጥላ ሥር የሚገኝ አንድ ሰው ፍትህ እስከሚያገኝ ድረስ በህይወት እንዲቆይ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ የመንግስቱ ኃላፊነት ነው። ለዚህም ሲባል ቀበቶው ተፈቶ፤ ሌሎች በራስ ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ነገሮች ሁሉ ተፈትሸው በዕስር ቤቱ ኃላፊዎች እጅ እንዲቆዩ ይደረጋል። ራሱን ገደለ የተባለው ኑረዲን ሃሰንም ቢሆን በማረሚያ ቤቱ ህግ መሠረት ተገቢውን ፈፅሟል።

ታዲያ እንደምን ሁኖ ኑረዲን ሃሰን ራሱን ሊያጠፋ ቻለ ለሚለው ጥያቄ የጉጅሌው ቡድን የሠራውን ያውቃልና የሆነውን አይናገርም።ወጣቱ ራሱን አላጠፋም። ኑረዲን ሃሰን ብርቱ የሆነ የመኖር ምኞት እና የራሱ ራዕይ የነበረው ወጣት ነበር። ይህን ወጣት ቀጥቅጠው ገድለው ተስፋውን ያጨለሙት የጉጅሌዎቹ ጀሌዎች መሆናቸውን ደርሰንበታል። የኑረዲን ሃሰንን ህይወት የቀጠፈው ግለሰብም ሆነ ቡድን ህወሃት በስልጣን እስካለ ድረስ ለፍርድ እንደማይቀርብ የታወቀ ነው። እንዲያውም በህወሃት ባህል መሠረት ተመስግኖ ይሾማል ይሸለማል እንጂ ሌላ የሚሆን ነገር አይኖርም። እንግዲህ ህወሃቶች ከሚገለጡበት ነውር ተግባራት መካከል አንዱ የንፁህ ደም ያፈሰሰን ነፈሰ ገዳይ ለሹመት ማብቃታቸው ነው።

እነዚህ ቡድኖች እግራቸው በረገጠበት መንደር ሁሉ የንፁሃንን ደም በከንቱ ያፈሳሉ። ይሄ የታወቀው ልማዳቸው ነው። የንፁህ ሰው ደም አፍስሰው ሲያበቁም ከበሯቸውን እየደለቁ እና ምድሪቷን እያስጨነቁ ማን ይደፍረናል እያሉም ያጓራሉ።

ከዚያም ለሌላ ዙር ግዲያ ያበረታታቸው ዘንድ፡

*ግደሉ ግደሉ ሰው መግደል ይበጃል፤*
*ሰው ያልገደለ ሰው ሲሄድ ያንጎላጃል።*

እያሉ የሰው ደም መጠጣት ለለመደው አምላካቸው ቅኔ ይቀኙለታል።

እኛ ግን እንዲህ እንላለን ለሁሉም ግዜ አለው። የፍርድ ቀንም ሩቅ አይደለችም።እንደ ኑረዲን ሃሰን በየቦታው ተገድለው የተጣሉ ኢትዮጵያዊያን ብዙ ናቸው። ብዙ ፍትህ ተነፍጓቸው በየሥፍራው እንባቸውን በመዳፋቸው የሚያፍሱ አሉ። ከነ ቤተሰቦቻቸው ሜዳ ላይ የተጣሉም አሉ። ብዙ ጆሮን ጭው የሚያደርጉ በህወሃት የተፈፀሙ ሰቆቃዎች ሁሉ ተመዝግበው በጃችን አሉ። እነዚህ ሁሉ ቀናቸውን እየጠበቁ ነው። የእነ ኑረዲን ሃሰን፤ የእነ ህፃን ነብዩ፤ የእነ ወ/ሮ እቴነሽ ይማም፤ የእነ ሽብሬ ደሳለኝ፤ የእነ አቶ ደራራ ከፈኒ፤የእነ አሰፋ ማሩ እና የሌሎች የብዙ ሺዎች ደም ከምድር ወደ ሰማይ እየጮኸ ነው። ይሄ ጩኸት መልስ የሚያገኝበት ቀን ፈጥኖ እንዲመጣ ትግሉ ተጧጥፎ በሁሉም መስክ መቀጠል ይኖርበታል። ሁል ግዜ እየገደልን እስከ መጨረሻው እንዘልቃለን ማለት ቅዥት መሆኑንም ለጉጅሌዎቹ ማስታወስ ተገቢ ይሆናል።

ጉጅሌዎቹ ብልህነት የሌላቸው ባይሆኑ ኑሮ የህዝብን ድምፅ ማድመጥ ይመርጡ ነበር። ከተዘፈቁበትም የቅዥት ዓለም ውስጥ ለመውጣት ምን እናድርግ ብለው ራሳቸውን ይጠይቁ ነበር። ግን ምን ያደርጋል ጉጅሌዎቹ ቅዠታቸውን እንደ ኃይማኖት አምነው ስለተቀበሉት ለሌላ እልቂትና ደም መፋሰስ ራሳቸውን ያዘጋጃሉ እንጂ ከገቡበት ቅዥት ለመውጣት ምን እናድርግ ብለው አይጠይቁም።ይሄ ቅዥታቸው ነው እኛ ከሌለን አገሪቷ ትበተናለች፤ የጎሳ ግጭት ይነሳል፤ እልቂት ይሆናል እያሉ ያለምንም እፍረት ድምፃቸውም ከፍ አድርገው እንዲለፈልፉ የሚያደርጋቸው። እውነቱ ግን በአሁን ሠዓት ከማንም በላይ ለአገራችን ቀንደኛ ጠላት መሆንን የመረጡት ራሳቸው ህወሃቶች ናቸው። የአገሪቷና የህዝቧ ጠላት መሆንን በመምረጣቸውም ነው ***"እኛ ከሌለን አገሪቷ ትበተናለች"*** እያሉ የሚያቅራሩት። ይሄንን ግን ባዶ ማቅራራት አድርጎ መገመት ከስህተት ይጥላል።

ህወሃቶች ሆይ ስሙ! በህዝባችን መካከል ያለው ልዩነት እና የጭካኔያችሁ ልክ ማጣት እስከ ዛሬ አቆይቷችኋል።ጭካኔንም ከጀግና ተግባር እየቀላቀላችሁ ተራራውን አንቀጠቀጥን እያላችሁ ያቅራራችሁትን ሁሉም ሰምቷችኋል። ህዝቡንም ድርና ማግ ሁነው በአንድነት ያቆዩትን ክሮች በጣጥሳችሁ ለመጨረስ ሌት ተቀን እንደምትባዝኑም የተሰወረ አይደለም።"*እኛ ከሌለን አገሪቷ ትበተናለች*" የሚባል ሟርትም ካልተገራው አንደበታችሁ መውጣቱንም በጥሞና አድምጠናል። ይሄ ቅዥታችሁ በቅዥት እንደሚቀር እኛ እንነግራችኋለን።እኛ ኢትዮጵያዊያን እያለን አገራችን አትበተንም። ምንም እንኳ የምትሰሩት ሁሉ የተራ ወንበዴ ተግባር ቢሆንም፤ ጭካኔያችሁ ወሰን ቢያጣ፤ ቅንጣት ታክል አገራዊ ኃላፊነት የማይሰማችሁ ብትሆኑም፤ በአገሪቷ ዜጎች መካከልም የጎሣ ግጭት ፈጥራችሁ በሚፈሰው ደም እጃችሁን ታጥባችሁ በኢትዮጵያዊያን ጫንቃ ለመቀመጥ ብትመኙም አይሆንላችሁም።

የህወሃት ፖሊሲ የሚቀየረው በመቃብራችን ላይ ነው እያላችሁ እንደምታላዝኑም እናውቃለን። ይሄ የህዝብ ጠላት መሆንን መምረጣችሁን የሚያሳረዳ ሌላው ዓቢይ ነገር መሆኑን እንዳትረዱ ድንቁርናችሁና ትዕቢታችሁ ስለጋረዳችሁ አታስተውሉትም። የአገር እና የህዝብ ጠላት መሆን ማለት "እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይበቀል" ብሎ ግትር ማለትን እንደሚጨምር ልናስታውሳችሁ እንወዳለን። "እኛ ያልነው ብቻ" ስትሉ ለእውነትና ለህዝብ ፍላጎት ሳይሆን ለራሳችሁ የግል ጥቅም እንደምትሞቱ ያሳየናል። አገርና ህዝብ ደግሞ ከግለሰቦችና እናንተን ከመሰለ እኩይ ቡድን ፍላጎት በላይ ስለሆነ በያዛችሁት መንገድ ብዙ አትዘልቁም። ህዝብ የአገሩ ባለቤት ለመሆን በተገኘው አጋጣሚ እና ባለው አቅም ሁሉ ይታገላችኋል። አሁንም ትግሉ እየተፋፋመባችሁ ነው። ከውስጥና ከውጪ የሚደረገው ትግል ከመቸውም ግዜ በላይ ተደጋግፎ የማይናወፅ መሠረት ጥሏል። "በመቃብራችን ላይ" ካለሆነ ብላችሁ ድርቅ ማለታችሁን የሰማ ሁሉ የአገሩ ባለቤት ለመሆን ጋሻና ጦሩን እያነሳ ነው። አሁንም ከግትርነታችሁ የማትመለሱ ከሆነ እድል ፈንታችሁ መሰበር ነው። እኛም ለዚያ እየተዘጋጀን ነው። ጀግና የሆነ በሊማሊሞ በኩል ይሞከረኝ ብሎ በገዛ ህዝቡ ላይ ጦርነት ያወጀው የጥፋት መሪያችሁ መለስ ዜናዊ በድንጋጤ ብቻ መሞቱን እናንተም እኛም ህያው ምስክሮች ነን። ከእናነት መንደር ፍርሃት እንጂ ጀግንነት የለም። ጀግና እኔ ብቻ ብሎ ድርቅ አይልም። ጀግና ከራሱ ጥቅምና ፍላጎት በላይ ለህዝብ የሞትለታል እንጂ ህዝብን አይገድልም። እናንተ እንደ ጀግና ለማሰብ የአስተሰሳብ ደረጃችሁ እጅግ በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል።

ጀግና እንደምን ያስባል ብትሉ ?

*ጀግና እንዲህ ያስባል እንላችኋለን "በሩቅም በቅርብም ያላችሁ ወዳጅና ጠላቶቻችን ሆይ ስሙ! እኛ ለኢትዮጵያዊያን ነፃነት፤ እኩልነት እና ፍትህ ስንል ማንኛውንም ዋጋ ለመክፈል፤ የህዝባችንን በደል ልንሸከም፤ሁሉንም መከራ ልንቋቋም፤ ለህዝባችን ነፃነት፤ እኩነልት እና ፍትህ የሚታገሉትን ልንደግፉ፤ ነፃነትን የሚከለክሉትን፤ በዜጎች መካከል ቂምና በቀልን የሚተክሉትን፤ ፍትህን የሚያዋርዱትን ለመዋጋት ቆርጠን ተነስተናል"*

( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## የወያኔ ፖሊሶች እራሳቸዉ ባሰሯቸዉ ሰዎች ላይ ሊመሰክሩ ነዉ

ከአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ጋር በተያያዘ በቡራዩ ተነስቶ የነበረውን ተቃውሞ መርተዋል የተባሉ 7 ወጣቶች ሰኔ 3 ቀን 2006 ዓም ፍርድ ቤት በቀረበቡበት ወቅት 5 ፖሊሶች እና አንድ የኢህአዴግ ባለስልጣን በእስረኞች ላይ ለመመስከር መቅረባቸው ታውቋል። በመዝገብ ቁጥር 48 ሺ 385 የተከሰሱት ፈይሳ አብዲሳ ገለታ፣ ፋይሳ ጉታ ረጋሳ፣ ታደላ ቶሎሳ ቱሉ፣ ሽሮምሳ ፋይሳ፣ ጆቲ ተመስገን፣ ከተማ ባሼ እና ስራታ ለታ ፍርድ ቤት ቢቀርቡም ዳኛው ሰአት ሄዷል በሚል ለሰኔ 17 ቀን 2006 ዓም ቀጠሮ ሰጥተዋል። ለምስክርነት የቀረቡት ፖሊሶች ኢንስፔክተር በለጠ በቀለ፣ ኢንስፔክተር ምትኩ ደሳለኝ፣ ኮማንደር አሰፋ ወልዴ፣ ፖሊስ አላና ተስፋ፣ ምክትል ኢንስፔክተር ደጀኔ ኪዳኔ ሲሆኑ፣ የቡራዩ የወጣቶች ቢሮ ሃላፊ የሆነው መስፍን ለማም በተከሳሾች ላይ ለመመስከር ቀርቧል።

አቃቢ ህግ ፖሊሶችን እና የኢህአዴግ ባለስልጣንን በምስክርነት ለማቅረብ የተገደደው ብዙዎቹ የአካባቢው ሰዎች በተከሳሾች ላይ ለመመስከር ፈቃደኛ ሆነው ባለመገኘታቸው ነው። አቃቢ ህግ በገንዘብ ምስክሮችን የመግዛት እንቅስቃሴ ቢጀምርም እስካሁን እንዳልተሳካለት የአካባቢው ሰዎች ይናገራሉ። ከዚህ ጋር በተያያዘ ሌሎች 3 ወጣቶች ምንም አይነት ክስ ሳይመሰረትባቸው በእስር ላይ እንደሚገኙ ታውቋል።

## ፖሊስ በሲኤም ሲ የቤት ለቤት ፍተሻ አካሄደ

ባየዉና በሰማዉ ሁሉ መደንበር የጀመረዉ የወያኔ አገዛዝ ባሳለፍነዉ ሳምንት ዉስጥ አዲስ አበባ ዉስጥ ከቤት ቤት እየዞረ የአዲስ አበባን ነዋሪ ሲያምስ መዋሉን ዝግጅት ክፍላችን ድረስ ስልክ የደወሉ ነዋሪዎች ገለጹ። በቀጥታ ከአዲስ አበባ የደረሰን መረጃ እንደሚያመለክተው ፖሊስ በእያንዳንዱ ነዋሪ ቤት እየገባ መታወቂያ የጠየቀ ሲሆን የውጭ አገር ዜጎች ደግሞ ፓስፖርት፣ ወደ አዲስ አበባ የገቡበት ቀን፣ የቀጣሪ ድርጅታቸውን ስምና አድራሻ፣ መታወቂያና ሌሎችንምየ ጥያቄዎች ተጠይቀዋል። ከዉስጥ አዋቂ ምንጮች በተገኘዉ መረጃ መሰረት ተመሳሳይ ፍተሻዎች በሌሎች አካባቢዎች ሊኖር እንደሚችል መረጃዎች ያመለክታሉ።

በቅርቡ የምእራብ መንግስታት አልሸባብ በኢትዮጵያ የሽብር ጥቃት ሊፈጽም እንደሚችል አስጠንቅቀው ነበር። መንግስትም 2 የአልሸባብ አሸባሪዎችን መያዙን አስታውቋል። አልሸባብ በሶማሊ ክልል 33 የመንግስትን ወታደሮች መግደሉ ይታወሳል። ይህንን አሰቃቂ ጥቃት ተከትሎ በመንግስትና በአልሸባብ ተዋጊዎች መካከል በተደረገው ጦርነት ከሁለቱም ወገን ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል። ይህ በእንዲህ እንዳለ የአሜሪካ መንግስት የዉጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት የሶማሌ ዝሪያ ያላቸዉን ዜጎቹን በተቻለ መጠን ወደ ኢትዮጵያ የሚያደርጉትን ጉዞ እንዲሰርዙ በመምከር ላይ መሆኑ ተሰማ። የአሜሪካ መንግስት ማስጠንቀቂያ ለምን እንደተሰጠ በግልጽ የሚታዉቅ ነገር ባይኖርም ጉዳዩ ከአልሸባብ ጋር የተያያዘ ነዉ የሚሉ ብዙ ወገኖች አሉ። የወያኔ ወታደሮችና አልሸባብ በቅርቡ ከፉኛ የተዋጉ ስለሆነና ብዙም ሰዉ ስለሞተ ወያኔ ይህንን ተከትሎ አጸፋዊ እርምጃ ይወስዳል የሚል ግምት አለ። ከዚህ በተጨማሪ አልሸባብም አዲስ አበባ ዉስጥ እርምጃ ይወስዳል የሚል ስጋት ስላለና ወያኔ ያየዉን ሁሉ እጁን እየጎተተ ስለሚያስር የአሜሪካ ስጋት ከዚህ ጋር የተያያዘ ሳይሆን እንደማይቀር ይገመታል።

## የወያኔ የጎሳ አጥር አሁንም ህዝብን እያጋጨ መሆኑ ተሰማ

ወያኔ የፈጠረዉ ኤትኒክ ፌዴራሊዝም ኢትዮጵያ ዉስጥ ብሄር ብሄረሰቦችን ከማግባባትና ከማቀራረብ ይልቅ የሚያጣላና የሚያጋጭ መሆኑን ብዙ መረጃዎች ያመለክታሉ። ባለፉት ሁለትና ሦስት አመታት ዉስጥ ብቻ ብዙ ኩታ ገጠም ብሄረሰቦች በድንበርና በኤኮኖሚ ጥያቄዎች ላይ ግጭት ፈጥረዉ በሰዉና በንብረት ላይ አደጋ ያደረሱ ሲሆን አሁን በቅርቡ ደግሞ በጎደሬ ወረዳ አካባቢ በምትገኘው ጻኑ ሃሙስ በምትባለዉ ወረዳ ሰኔ 5 ፣ 2006 ዓም የተነሳው ግጭት ለበርካታ ዜጎች መፈናቀል ምክንያት መሆኑን ከአካባቢው የደረሰን መረጃ ያመለክታል።

የወረዳው ባለስልጣናት ከክልሉ ውጭ የሚኖሩ የሌሎች አካባቢ ተወላጆችን አካባቢውን ለቀው እንዲወጡ ማዘዛቸውን የሚናገሩት ምንጮች፣ በረካታ ነዋሪዎች ተፈናቅለው በአሁኑ ጊዜ ቴፒ ከተማ ውስጥ ሰፍረው እንደሚገኙ ታውቋል። በግጭቱ ምን ያክል ሰዎች እንደተጎዱ ባይታወቅም አንድ ፖሊስ መገደሉን የአካባቢው ምንጮች ገልጸዋል።የፌደራል እና የክልል ፖሊሶች በአካባቢው የፓትሮል ቅኝት እያደረጉ ሲሆን፣ ማንኛውም አይነት እንቅስቃሴ ተቋርጧል።

ግጭቱ የተነሳው የወረዳው ባለስልጣናት ጻኑ የሚባለው በደቡብ ክልል ስር የሚገኘው አካባቢ የጋምቤላ መሬት ነው የሚል ጥያቄ ማንሳታቸውንና ከሌሎች አካባቢዎች የመጡ ሰዎችን በማስወጣት የአካባቢውን ተወላጆች ለማስፈር በመፈለጋቸው ነው። የጋምቤላ ክልል ሰፋፊ መሬቶች ለውጭ ባለሀብቶች እና ለህወሃት የቀድሞ ታጋዮችና በስልጣን ላይ ላሉ የመከላከያ ሰራዊት አዛዦች በስፋት መሰጠቱን ነዋሪዎች ይናገራሉ። እስካሁን ድረስ ምን ያክል ሰዎች እንደተፈናቀሉ በቁጥር ለማወቅ የተደረገው ጥረት አልተሳካም። አካባቢው በቡና ምርቱ የሚታወቅ ሲሆን፣ በርካታ የደቡብ፣ የአማራና የሌሎች ብሄረሰቦች ተወላጆች ይኖሩበታል።

## በአጋዚ ጦር በግፍ የወደቁት ወገኖቻችን ቀን

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

**ሳምንታት ከመለስተኛ** የጦር አውድማ ጋር ትመሳሰል እንደነበር የሚናገሩ ጥቂቶች አይደሉም። በጊዜው የለምንም የፍርድ ሂደት ከመጉላላት፣ መደብደብ፣ መታሰርና መሰደድ ጀምሮ ክቡር ሂዎትን እስከማጣት የደረሰ ሰቆቃ በሕዝባችን ላይ መፈጸሙ መቼም ቢሆን የማንረሳው የህዘን ትዝታችን ነው የሚሉት በዝክረ ሰማእታቱ ላይ የተገኙ ታዛቢዎች "ገፍን አንቀበልም ብለው የተሰዉትን ስናስታውስ እኛም ዛሬ ግፍን ተሸክመን ላለመቀጠል ቃል መግባት ይጠበቅብናል" ማለታቸውም ተያይዞ ተጠቅሷል።

ከድፍን 9ኝ ዓመትም በኋላ በግፍ ያለፍርድ የወደቁት ወገኖቻችን ፍትህን አላገኙም ያሉት ሌላው ታዛቢ ደግሞ፤ ይህን ፍትህ ከወያኔ መጠበቁ ከእባብ እንቁላል እርግብ እንደመፈለግ ያለ ነው ስለሆነም ወገኖቻችን ያጡትን ፍትህ ለማስመለስም ሆነ የተደፈረውን ማንነታችንንና የተገፈፈውን ነጻነታችንን ለማስከበር አንድ ሆነን በመቆም ለጠንካራ ትግል ቆርጠን ስንነሳ ነው ብለዋል።
ባለፉት የወያኔ የግፍ አገዛዝ ዓመታት በተለይም ከ1997 ምርጫ ወዲህ አገዛዙን ለመጣል ጎልተው የታዩ ትብብሮችና መግባባቶች እምብዛም ናቸው የሚሉት እኒሁ ታዛቢዎች ልዩነታችንን ከማጉላት ይልቅ አንድ በሚያደርጉን ላይ በመተባበር ትልቁን የጋራ ጠላታችን የሆነውን ወያኔን በማስወገዱ ላይ ማተኮር ነበረብን ነገር ግን ይህ እምብዛም ሲሆን አይታይም ካሉ በኋላ ብዙ ጊዜ ግን ትብብሩ ወደፊት ምን ሊሆን ይችላል በሚል ምናባዊ መላምት ላይ በመጨቃጨቅ ዋናውን ጠላት ወያኔን እንረሳለን፤ ይህ ሊቆም ይገባዋል ብለዋል።

የ1997ቱን ምርጫ ተከትሎ በተከሰተው የወያኔ አጋዚ ጦር ጭካኔ የተሞላበት ጭፍጨፋ ወያኔ ባመነው እንኳ ከሁለት መቶ ያላነሱ ንጹሃን ወገኖቻችን በጥይት ተደብድበው መገደላቸው ይታወሳል።

## ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

**ማርቲን በሲሁ ንግግሩ** እስክንድር በእስር ቤት እየደረሰበት ያለውን ስቃይ እና የቃሊቲ እስር ቤትን አስከፊና አስቀያሚ ገጽታዎች በበቂ ሁኔታ ለታዳሚዎቹ አሳይቶአል። እስክንድር ህግን ጥሰህል ተብሎ ለእስር የተዳረገው መንግስትን በመተቸቱ እንደሆነ ሳው ማርቲን፤ "ይህ የሚያም ቀልድ ነው"ብሎ አል። "ይህ የጎልደን ፔን ሽልማት፤ ከ1000 ቀናት በላይ በእስር ላሳለፈው ለእስክንድር ነጋ ብቻ ሳይሆን እስክንድርን ለእስር ለዳረገው ለጋዜጠኝነት ሙያ ጭምር የተሰጠ ክብር እንደሆነ ይሰማኛል" ሲልም ለሽልማቱ ያለውን አክብሮት ገልጾአል። እስክንድር በአካል ከደረሰበት ቅጣት በላይ ከቤተሰቡ እና ከሚወደው ብቸኛ ልጁ በመለያዬት የደረሰባት የመንፈስ ቅጣት የከፋ እንደሆነም ማርቲን አመልክቱዋል። እስክንድር የተማረ እና በሌላ ሙያ ሊሰማራ እየቻለ በጨቂዋኞች እጅ እየተሰቃየ የሚገኘው ለእውነት ባለው የጸና አቂዋም እና ለሀገሩ ባለው ፍቅር ምክንያት እንደሆነም ገልጾአል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አ<u>ጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፐሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## በአዲስ አበባ የህዝብ መፈናቀል

. . . ( ከገጽ 3 የዞረ )

የመክፈል፣ በአንዳንዶቹም የማፍረስ ሥራዎች እየተከናወ ኑመሆኑን ምንጮቹ ጠቅሰዋል። አስተዳደሩ በመልሶ ማልማት ፕሮግራሙ በተለይ የቀበሌ ቤቶች ውስጥ የሚኖሩ ነዋሪዎችም ክየኮንዶምኒየም ቤት የሚሰጥ ቢሆንም በወቅቱና በሰዓቱ የሚከናወን ባለመሆኑ ነዋሪዎች ለእንግልትና ለተጨማሪ ወጪ እየተዳረጉነው።

በተለይ የግል ቤቶች ምትክ ቦታ በተመሳሳይ ሁኔታ በፍጥነት የሚከናወን አለመሆኑ፣ በቂ የዝግጅት ጊዜ ሳይሰጥ ነዋሪዎች እንዲነሱ መገደዳቸው በየአካባቢው ያላቸውን ማህበራዊ ትስስር የሚያናጋና ልጆቻቸውንም ትምህርታቸውን ለማስቀጠል የሚቸገሩበት ሁኔታ ተፈጥሮአል። በተለይ በግለሰብ ቤቶች ተከራይተው የሚኖሩ በርካታ ነዋሪዎች በምትክ ቤቶች አሰጣጥ ውስጥ የማይካተቱ መሆኑ ማህበራዊ ቀውስ እየፈጠረ እንደሚገኝ ታውቋል።

የከተማ አስተዳደሩ በተለይ በሊዝ ጨረታ ቦታዎችን አወዳድሮ ሲሰጥ የመሬት አቅርቦቱ እጅግአነስተኛ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በአንድ ካሬ ሜትር 10ሺ ብር እና ከዚያ በላይ የሚሰጡ ጥቂት ሐብታሞች ተጠቃሚ የሚሆኑበት፣ በአንጻ አነስተኛና መካከለኛ ገቢዎች ያላቸው ነዋሪዎች የማይጠየቁበት ሥርዓት መፈጠሩ ይታወቃል። የኢህአዴግ መንግስት እጅግ በውድ ዋጋ የሚሸጠው መሬት በሙስና እየተበላ መሆኑንም የሚደረሱት መረጃዎች ያመለከታሉ። የኢሳት ምንጮች እንደሚገልጹት ከመሬትና ከታክስ ጋር በተያያዘ በአዲስ አበባ ከፍተኛ የሆነ የዝሪፊያ መረብ የተዘረጋ ሲሆን፣ ምርጭ የሚባሉ ቦታዎች በእነዚህ ጥቂት ግልሰቦች እጅ እየገባ ነው። እነዚህ ሰዎች ገቢዎችንና ጉሙሩክን ከጀርባ ሆነው በመቆ|ጣጠርና ስራቸውን በንጽህናና በሃቀኝነት የሚሰሩ ሰራተኞችን በተለያዩ ወንጀሎች በመክሰስ ከስራ እንዲባረሩ በማድረግ ከፍተኛ ሃብት እየመዘበሩ መሆኑን ምንጮች አክለው ገልጸዋል። ታክስ ማጭበርበርና መሬት በህገወጥ መንገድ መዝረፍ በኢትዮጵያ አቋራጭ የመክበሪያ ስልት እየሆነ ነው።

## የኑረዲን ሃሰን ደም በከንቱ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የጀግና ሃሳብ እንዲህ ነው። እናንተ ግን እንዲህ ታስባላችሁ ብለን አንጠብቅም። ይሄ አስተሳሰብ ተፈጥሯችሁም ባህላችሁም አይደለም።ከግል ጥቅማችሁ ዘላችሁ ለእውነትና ለህዝብ ክብር የመቆም ባህል በእናንተ ውስጥ የለም። በእናንተ ውስጥ ያለው "ተኛ ሲባል የሚተኛ፤ ተነስ ሲባል የሚነሳ "ከንቱ ዜጋ የመፍጠር ምኞት ነው። ይሄን ምኞታችሁን የሚያመክን ወጣት እምቢ ብሎ ተነስቶ በግንቦት ሰባት ለፍትህ፤ ነፃነትና ለዴሞክራሲ በሚደረገው ትግል ውስጥ እየተቀላቀለ ነው። እኛ እያለን አገራችን አትበተንም የሚሉ ተነስተዋል። ከእንግዲህም አታስቆሟቸውም። በመቃብራችን ላይ ብላችሁ እንደተመኛችሁት ሁሉ ምኞታችሁን ለማስፈፀም መሠረት የያዘ ትግል በሁሉም አቅጣጫ ተጧጥፎ ይቀጥላል።

በመጨረሻም ያፈሰሳችሁት ደም ከምድር ወደ ሰማይ እየጮኸ ነው። ብዙ ኢትዮጵያዊያንን እየገደላችሁ በጅምላ በየጉድባው እንደምትቀብሩም ታውቋል። ይሄን ሁሉ ግዲያ እንድትፈፅሙ የሚያደርጋችሁ የስልጣን ሥሥትና የንዋይ አፍቆሮታችሁ የሚርካ አልሆነም። እንግዲህ ለዚህ ሁሉ ወንጀል ተጠያቂው የትግሬ ነፃ አውጪ ነኝ ብሎ ራሱን የሚጠራው ጎጠኛው ቡድን መሪዎች ናቸው። በዚያች አገር የሚፈሰው የኢትዮጵያዊ ደም ሁሉ ካለእነርሱ እውቅናና በጎ ፈቃደኝነት ውጪ አይደለም። ለእያንዳንዷ ላፈሰሳችሁት ደም ዋጋ የምትከፍሉበት ቀን እሩቅ አይደለም። በህይወት እያላችሁ ታያላችሁ ልጆቻችሁም ምስክሮች ይሆናሉ።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**